# ቅጣት

Adelheid Marie Bwire
Melany Pietersen
Dawit Girma
2
አማርኛ am

አንድ ቀን እናቴ በጣም ብዙ ፍራፍሬዎች አመጣች።

መቼ ነው ታዲያ ከፍራፍሬው የምትሰጭን? ብለን ጠየቅን።
‹‹ፍራፍሬውን ማታ እንበላዋለን።›› አለች እማ።

ወንድሜ ራሂም ስግብግብ ነው። ከሁሉም ፍራፍሬ ቀመሰ።
አብዛኛውንም እሱ በላው።

‹‹እዩ እዩ ራሂም ምን እንዳደረገ!›› ታናሹ ወንድሜ ጮኸ።

‹‹ራሂም ክፉ እና ራስ ወዳድ ነው›› አልኩ እኔ።

እናታችን በራሂም ድርጊት ተናደደች።

እኛም በራሂም ተናደንበታል። ነገር ግን ራሂም ምንም አልመሰለውም።

‹‹ራሂምን አትቀጬውም?›› ሲል ትንሹ ወንድሜ ጠየቀ።

‹‹ራሂም፣ ቶሎ ብለህ ይቅርታ ጠይቅ›› እናታችን አስጠነቀቀችው።

ራሂምም ወዲያው ይታመም ጀመር።

‹‹ሆዴን በጣም አመመኝ›› በማለት ራሂም አልጎመጎመ።

እናታችን ይህ ሊከሰት እንደሚችል ታውቅ ነበር። ፍራፍሬው ራሂምን እየቀጣው ነው።

በኋላም ራሂም ይቅርታ ጠየቀን። ‹‹ከእንግዲህ ዳግመኛ ስግብግብ አልሆንም›› በማለት ቃል ገባ። ሁላችንም አመንነው።

# Global Storybooks

globalstorybooks.net

## ቅጣት


Adelheid Marie Bwire
Melany Pietersen
Dawit Girma


CC BY